
ስብሀት ገብረእግዚአብሄር

# የትረካ ጥበብ

(ከ1966 - 2003 ዓ.ም)



ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር

# የትረካ ጥበብ

(ከ1966 — 2003 ኢ.ም)

አርትኦት፡- አቤል ሠይፈ እና
ማንይንገረው ሸንቂጥ

© 2013 - የቅጂ መብቱ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ እትም - ጥር 2013
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

## የደራሲው ሌሎች ስራዎች

- አምስት ስድስት ሰባት
- ትኩሳት
- ሌቱም አይነጋልኝ
- ሰባተኛው መልአክ
- እግረ መንገድ ፩ እና ፪
- እነሆ ጀግና
- የፍቅር ሻማዎች
- ዛዚ
- ቦርጨኬቅ!

አሣብ አሳታሚ
Hassab Publishers
ስ.ቁ. +251-936 959 644 / +251-978 106 538
Email - hassabpublishers@gmail.com

# የአሳታሚው ማስታወሻ

አሳብ አሳታሚ የደራሲ ስብሀትለአብ ገብረ እግዚአብሄርን የተለያዩ የስነ ፅሁፍ ስራዎች፣ ላለፉት አስራ ሶስት አመታት ግድም ለህትመት እንዲበቁ አድርጓል። *አምስት ስድስት ሰባት፣ ትኩሳት፣ ሌቱም አይነጋልኝ፣ ሰባተኛው መልአክ፣ እግረ መንገድ፣ እነሆ ጀግና፣ ዛዚ እና ቦርጩቅ!* የተባሉት ረጃጅም፣ ቢሳና አሜሞር ልብወለዶቹ በተደጋጋሚ እየሳተመ ለአንባብያን ሲያቀርብ ቆይቷል።

ደራሲው *እግረ-መንገድ* በሚል በ*አዲስ ዘመን* ጋዜጣ የፃፋቸው ፅሁፎች፣ በደራሲና ጋዜጠኛ ደምሴ ፅጌ አርታኢነት በሁለት መፅሀፎች ማለትም ቅፅ አንድ እና ቅፅ ሁለት ተብለው እንደተዘጋጁ ይታወቃል። እነዚህን ሁለት ቅፆች አሳብ አሳታሚ በአንድነት ጠርዞ በየካቲት 2011 ዓ.ም. በድጋሚ ለንባብ አብቅቷል።

አሁን ደግሞ በሰፊ የጊዜ ወሰን (ከ1966-2003) ደራሲው ከፃፋቸው በርካታ መጣጥፎች ውስጥ በዚህ መድብል ስድሳውን መርጦና ሰድሮ *የትረካ ጥበብ* በሚል ርዕስ አበርክቶላችኋል።

ወደፊትም ጊዜና ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን ዘመኑን ሙሉ የተጋውን፣ የደራሲያችንን የብእር ትሩፋት ለትውልድ እንዲተላለፍ በተለያዩ ቅፆች በተከታታይ ለማቅረብ ተስፋና ምኞት ሰንቀናል። አማልክቱ ከረዱን (እንዲል ስብሀትለአብ)፣ ከአቅም በላይ ካልሆነብን በቀር አንቦዝንም።

ይህንን ስብስብ በማዘጋጀት ሂደት እገዛ ያደረጉልን ሁሉ ልባዊ ምስጋና

ይድረሳቸው፡፡ በተለይ ሀይለጊዮርጊስ ማሞ፣ ማንደንገረው ሸንቁጥ፣ ቃልኪዳን ታደሰ፣ ብሩክ መኮንን ተክለየስ፣ አለማየሁ ገላጋይ፣ ኢዮብ ካሳ፣ እንዳለጌታ ከበደ፣ ዘነበ ወላ፣ የሺወርቅ ወርቁ፣ ጌታቸው ወርቁ ---- ለቀናና ልባዊ ትብብራችሁ እጅግ ትመሰገናላችሁ፡፡

መልካም ንባብ

አቤል ሠይፈ

የአሳብ አሳታሚ ባለቤት

# መግቢያ

"ብዙ ጊዜ የምናስታውሰው ካለማስታወስ ወይም አሳስተን ለማስታወስ በምናደርገው ልፋት ይመስላል። ይሄ ግጭት አስገራሚ ነው። በሦስት ገጽ ሰበብ አራት መቶ ገጽ ማጠፋፋት፣ ከአንድ በቸልታ ከተሰጠ አስተያየት ርዕዮት ገንብቶ ሰፊ ፋይዳን ማክሰም ያሉብን ፀባዮች ናቸው። ትውስታን አሳስቶ ማቅረብ፣ ትውስታን በርዞ ማቅረብ፣ ትውስታን ሆን ብሎ ማጥፋት በአገራችን የኪነጥበብ መልክዓምድር ላይ ይታያሉ። ምክንያታቸው ግላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ስሜታዊ ሊሆን ይችላል። በአያያዛችን አረፍ አንመስልም።"

አዳም ረታ

*(የስብሐት ተረቶች ትዝታ - በመልክአ ስብሐት መጽሐፍ ውስጥ)*

ስብሐት ከጻፋቸውና ለህትመት ከበቁት ረዣዥምና አጫጭር ልብወለዶቹ በተጨማሪ በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች የወጡት መጣጥፎቹ ምናብ ሰፊውን፣ አሰላሳዩንና አጫዋቹን[1] ደራሲ እንዳንዘነጋ አስተዋፅዖቸው ከፍተኛ ነው። በሕይወት ዘመኑ ካበረከተልን መጣጥፎች 60 ያህሉን በዚህ መድብል እነሆ ብለናል። ከላይ የተጠቀሰውና አዳም ረታ *"በአያያዛችን አረፍ አንመስልም"* በሚል የሚወጋበትን፣ ትውስታን ሆን ብሎ የማጥፋት አሊያም የመበረዝ አጉል አባዜያችንን ለመቅረፍ፣ ይህ መድብል አጋዥ እንደሚሆን በልበሙሉነት መመስከር ይቻላል።

---

1 "እኔ እውነቱን ነው የምልህ፣ ጨዋታዎች መጻፍ ነው ፍላጎቴ። አሁን እየተጨዋወትን አይደል? .....እንደዛ በቃ። ሰው ጨዋታ ይፈልጋል። የሚያጫውት ነገር ልጽፍለት ብዬ ነው የምጽፈው። ኢንተርቴይነር ይባላል። አጫዋች...."

*ስብሐት ከኢንፎቴይመንት መጽሔት ጋር ያደረገው ቃለምልልስ*

እያንዳንዱ መጣጥፍ የተገኘበ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ እንደወጣ ባይጠቀስም፡[2] የተጻፉበት ጊዜ ለጠቀስ የሚገዙ የአንዳንዶቹ ጽሑፎች ብቻ መቼ እንደተጻፉ በጽሑፎቹ መጨረሻ ሥፍር ይገኛል። ይህም ጽሑፎቹን ከዘመኑ ጋር አቆራኝተን እንድናሰላስለው ይረዳናል።

ሌላው ጉዳይ፡ ስብሐት የራሱ ወጥ የሆነ የሆሄያትና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም አለው። በዚህ መጽሐፍ ይህንኑ ለመጠበቅ ጥረት ተደርጓል። አንባቢ ወደ መጣጥፎቹ ሲዘልቅ ይህን እንደሚገነዘብ እርግጥ ነው።

በዚህ ስብስብ ውስጥ ሃይማኖት-ነክ፡ አፈ-ታሪክ፡ ታሪክ፡ ፍልስፍና ቀመስ ወግ፡ ሳይንስ፡ የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ፡ ማኅበራዊ ትዝብት ... በውብ ቃላት እየፈሰሱ፡ እያዝናኑንና እያብሰለሰሉን የሚዘልቁ ትረካዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። አደራደራቸው ተመሳስሎን በጠበቀ መልኩ እንዲሆን በተቻለ መጠን ተሞክሯል።

በተለያየ ጊዜና ዘመን የተጻፉ ቢሆንም፡ አንባቢን የማይጎረብጥ፡ ቀለል ያለና አዝናኝ የአተራረክ ዘይቤ ወጥ በሆነ ሁኔታ ማስተዋላችን፡ ደራሲው ስብሃት ለተራኪነት የተፈጠረ ለመሆኑ አስረጅ ነው። አንድ ጉዳይ እንዴት ተከሰተ ከሚለው በላቀ፡ እንዴት ተተረከ የሚለው ጉልህ ተጽዕኖ እንዳለው ለመናገር፡ የመጣጥፎቹን ማራኪነት ምስክር አድርጎ ማቅረብ ይቻላል። ሰፊ አሳብ የያዘን ዘርፌ ብዙ ዕውቀት የሚዳስስ ጽሑፍ እንዲህ በቀለለ መልኩ ለማቅረብም፡ በጥልቀት የገባው መሆንን ይጠይቃል። "አቅልለህ ልታቀርበው የምትችለው፡ በጥልቀት ስትረዳው ነው" የሚለውን አባባል ያፀናልናል።

በንባብ ጉዟችን በደራሲው የምናብ ስፋት ብቻ ሳይሆን፡ ዘርፌ ብዙ ጥልቅ አንባቢነትና አስታዋሽነት መደነቃችን አይቀርም። ለነዚህ መሰል ትረካዎች የተጋለጠ አንባቢ አንዳንድ የሳይንስ፡ የሃይማኖት፡ የፍልስፍና እሳቤዎችን በበለጠ ለማወቅ እንደሚነሳሳ ቢገመት፡ ከእውነታው እምብዛም የራቀ አይሆንም። እና ታዲያ፡ ምን እንጠብቃለን? እንጀምራ!

ማንይንገረው ሸንቁጥ (አርታኢ)

---

[2] ጽሑፎቹ የተወሰዱት ከአዲስ ዘመን፡ አዲስ አድማስ፡ ኔሽን፡ እፎይታ፡ ነጋድራስ [illegible] ጋዜጦች እና የካቲት፡ መነን፡ ዜን ከተባሉ መጽሔቶች ነው - አሳታሚው።

# ማውጫ

1. የተከበረው እንግዳ ............................................11
2. ሰው ..........................................................18
3. ሰውና ማስመሰል ...............................................22
4. ስሞችና ቁጥሮች ..............................................28
5. አበደት በየአይነቱ ...........................................34
6. መተጋገዝ ....................................................49
7. ስልጣን በየፈርጁ ............................................54
8. የሆነም ያልሆነም ............................................63
9. አበረን እንፈላሰፍ ..........................................67
10. አንዳንድ ነጥቦች ስለ ኤግዚስተንሺያሊዝም ..................79
11. ጓደኝነት በየአይነቱ ........................................95
12. ከዳኞቸው ወርቁ ጋር ........................................110
13. በአሉን እስከማውቀው ......................................116

14. እንደ ልቡ የኖረና የጻፈ አርቲስት ........ 123
15. ዘነበች ጭራ ቀረሽ- በሕይወት መድረክ ........ 130
16. ቁማርተኛው ዶስቶቭስኪ ........ 136
17. ፍቃዱ ተክለማርያም ........ 141
18. ሲግመንድ ፍሮይድ ........ 151
19. አለቃ የኋላሸት የሳቅና የጅቡዱ አባት ........ 155
20. ዝምቡና ሸረሪት ........ 160
21. አለማዊው ያሬድ ማህሌታይ ........ 165
22. ጊዜን ስናስተውለው ........ 170
23. ዝንጅሮዎቹ ........ 180
24. የሰው ዝርያ ሂደት ........ 186
25. አዲስ አበባ - በርቀት ........ 193
26. እውነት ከምድር እንዴት እንደጠፋ ........ 196
27. የጠላት ትልቅ የለውም ........ 203
28. የጠላትና የእሳት ትንሽ የለውም ........ 214
29. ቡና ውጉዝ፣ ትምባሆ ውጉዝ ........ 221
30. አዳምና ሄዋን ........ 227
31. እነሆ ቁጠባ ........ 231
32. ተጓቸሮ- ዘወትር እንግዳ ........ 236
33. እነሆ እንደ ወቅቱ ........ 241
34. እጆች ........ 245

35. የ13 ቁጥር ትውስታ ........................................ 251
36. ምስለ ምሳሌ ........................................ 255
37. ሸሀዩ ናድ ይላል ምድር ........................................ 257
38. መይሳው! ........................................ 261
39. ኦሮ በተረት መልክ ........................................ 268
40. ሊበችና ሊሎቻችን ........................................ 271
41. ወርቅ! ወርቅ! ወርቅ! ........................................ 276
42. የሽመና ጥበብ በጥንት ዘመናዊ እይታ ........................................ 282
43. የትረካ ጥበብ ........................................ 287
44. የሱፊና የዜን ትረካዎች ........................................ 291
45. የዜን ቡዲዝም ትረካዎች ........................................ 300
46. ክርስትናችን በስነጥበብ ቅኝት ........................................ 303
47. ክርስትናችን እንደስነጥበብ ምንጭ ........................................ 309
48. ቅድስት አገር በታሪክ መድረክ ላይ ........................................ 314
49. አማልክትና ሰዎች ........................................ 325
50. ሀበሻና ምክር ........................................ 333
51. ይሉኝታ ........................................ 336
52. ሀበሻና ይሉኝታ ........................................ 340
53. መዕዋቾች ........................................ 343
54. የማህበረሰብ ጥበብ ........................................ 347
55. ባህል እንደቀንበር ........................................ 350

56. ባህል እንደ ኩርኩም ........ 353
57. መንግሥት ብቻ ሳይሆን እኛም መለወጥ አለብን ........ 356
58. ቁም ነገራዊ ሃሳብ ........ 367
59. የጥበብ ያለህ! የሰሚ ያለህ! ........ 370
60. ጆሮ ያለው ይስማ ........ 380

# የተከበረው እንግዳ

ለተከበራችሁ አንባብያን፣ በተለይ እና በጣም በተለይ፤ እሳት ለላሰው ነፃ ትውልድ አባላት፣ እነሆ ትረካ በያይነቱ!

የተከበረው እንግዳ ማንነቱ ምስጢር ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚመጣው አመሻሽ ላይ፣ ከብቶቹና በግ ፍየሎቹ ረጃጅም ጥላዎቻቸውን አስቀድመው ወይ አስከትለው ወደየማደሪያቸው ሲሰባሰቡ ነው።

እንደ ቋንቋው እንዳገሩ አባባል ይለያይ እንጂ፣ የተከበረው እንግዳ ሲመጣ የሚለው ግን ያው፣ "የመሸብኝ እንግዳ ነኝ፣ አሳድሩኝ" ነው።

"ይግቡ፣ ቤት ለ"እንግዳ" ብለን እንቀበለዋለን። የገባውን ጭቃ ወይ አፈር እንዲገላገል አስታጥበነው አዘናንተነው እንደአቅማችን እራት እንጋብዘዋለን። ሙከት ወይም ጠቦት ልናርድለት እንችላለን ወይም ከኛ ጋር ጎመኑን በልቶ ያድራል። የምናቀርበው ሥጋም ይሁን ጎመን፣ ለማን እንደሆን አናውቅም (እንግዳችንም ሊያውቀንም ላያውቀንም ይችላል)። ከእራት በኋላ ነው እንግዳችን ማን እንደሆነ፣ ከየት እንደመጣ፣ ወዴት እንደሚሄድ፣ ጉዞው ላይ ምን ምን እንዳጋጠመው መጠየቅና ማወቅ የሚፈቀድልን። ይህ ስርአት ከሰው ልጅ ብዙ ጥበባት አንዱ ነው።

የጥቂት አስተዋይ ሰዎች ጉዞ አንዳንድ ጊዜ ለብዙ (ለሚሊዮኖችም) የሰው ልጆች ብዙ ጥቅም ይሰጣል። ስለዚህ ጉዞ ላይ ያለውን ሰው እንደ ቅዱስ በመቀበልና በጥሩ ሁኔታ በማስተናገድ የተጓዦችን ሰዎች ህይወት

‹‹ስብሐት ገ/እግዚአብሔር የሚለየው በአይጎረብጤ ብዕሩ ነው፤ ብዕሩ ከኢየሱስ ምሕረትን የተማረች ነች፤ እንደ ክርስቶስ ሰምራ ሰይጣን እስከ መውደድ የደረሰች፣ ገሀነም ገብታ፣ እንኳን ሊያቃጥላት የማይሞቃት ነች፤ እንደ ሀኒባል አንዳይናው ጀግና የኤልፐስ ቅዝቃዜ የማያኮማትራት - - -››

አሌክሳንድሮቭ ገላግሎቭች

ኔሽን ጋዜጣ ቅፅ 1 ቁ. 83 ጥር 1996

‹‹ስብሐት አንድም ሦስትም ነው! ደራሲ፣ አዋቂና ነገር-አዋቂ። ጋሽ ስብሐት ካስተማረን ነገሮች አንዱና ዋነኛው ድፍረት ይመስለኛል። ባዶ ድፍረት ሳይሆን የሥነ-ጽሑፍ ድፍረት። ቁምነገር ያዘለ ድፍረት። ውበት ያለው ድፍረት። ዕውቀት ያለው ድፍረት። ይህንን ዓይነቱን ድፍረት ደግሞ - - - አንድም በመማር፣ ሁለትም በማንበብ፣ ሦስትም በመኖርና በመብሰል የሚያገኙት ነው። ስብሐት እነዚህ ሦስት ነገሮች ካሏቸው ጥቂት ደራሲያን አንዱ ነው። ከሦስቱ ነገሮች እጅግ የሚጠናበት ደግሞ ማንበቡ ይመስለኛል። ማንበብ ቢሉም ሥር የሰደደ ማንበብ ነው - መመራመር፣ ማውጠንጠንና ማስታወስ የታከለበት። ከነዚህ ከሦስቱ ደግሞ የጋሽ ስብሐት የጠና ችሎታው ማስታወስ ይመስለኛል። ጋሽ ስብሐት እንግዲህ አንድም ሦስትም ነው ስል እንዲህ እንዲህ ያሉትን ጠባዮቹን ከቁጥር ውስጥ በማስገባት ነው።››

ነቢይ መኮንን

አዲስ አድማስ ጋዜጣ፤ የካቲት 17፣ 2004

0118278460

አሳብ አሳታሚ
Assab Publishers
+251-936 959 644 / +251-978 106 538

ዋጋ 250.00 ብር
ዋጋ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር

የሽፋን ገጽ ቅንብር፡ 0923 28 04 19